Washington Apple Health

# ለዋሽንግተን አፕል ጤና (Apple Health (Medicaid)) የመጀመሪያ-ጊዜ ተጠቃሚዎች መመሪያ

ክፍል 1፤ እርስዎ በApple Health ከተመዘገቡ በኋላ ስለ Apple Health ሽፋን እና እንዴት የመጀመሪያ ቀጠሮውን እንደሚይዙ ለማወቅ ይህንን መመሪያ ይጠቀሙ።

ክፍል 2፤ የመጀመሪያ የጤና እንክብካቤ ቀጠሮዎን ለመያዝ መረጃን (**በዚህ መመሪያ ክፍል 2 ይመልከቱ**)።

## ክፍል 1፡ እርስዎ በApple Health ከተመዘገቡ በኋላ

የእንኳን ደህና መጣቹህ ቡክሌት ጨምሮ ደብዳቤ እንልክሎታለን፡ ፡ ቡክሌቱ ሽፋኖን የሚመለከቱ ኣስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ ነው። ቡክሌቱን መስመር ላይ ይመልከቱ **hca.wa.gov/ah-client-booklets** ። የጤና እቅድዎ ደግሞ ስለ ጥቅምዎችዎ መረጃ ይልክልዎታል።

በአፕል ጤና (Apple Health) በተሳታፉ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ የ ProviderOne አገልግሎቶች ካርድዎን ይቀበላሉ። ይህንን ካርድ ይያዙ። ካርድዎም ለእርስዎ ከመላኩ በፊት እንዲሰራ ይደረጋል።

እያንዳንዱ በ Apple Health የተሳተፉ የቤተሰብዎ አባልም የራሳቸውን ካርድ ያገኛሉ። ካርድዎም በህይወትዎ ዘመን ከእርስዎ ጋር የሚቆየውን የደንበኛ ቁጥር ያሳያል። የጤና አገልግሎቶችን ለማግኘት ይህ ቁጥር ያስፈልግዎታል።

ከዚህን በፊት የApple Health ካለዎት አዲስ ካርድ አንልክልዎትም። የበፊት ካርድዎ አሁንም የሚሰራ ሲሆን፣ የደንበኛ ቁጥርም ያው ተመሳሳይ ይሆናል።

### እርስዎ ካርድ ካልተቀበሉ

ለሽፋን ካመለከቱበት ከሁለት ሳምንት በኋላ ካልደረሰዎ ወይም ካርድ ከጠፋብዎ፣ ProviderOne አገልግሎቶች ምትክ እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ።

በ WAPlanfinder mobile app በኩል የአገልግሎት ካርድዎን የድጂታል ኮፒ ማግኘት ይችላሉ። አፑን ለማውረድ፡ **wahbexchange.org/mobile/**

ምትክ ካርድ የምጠየቁበት ብዙ መንገዶች አሉ፡

- የደንበኛ ድረ-ገፅን ይጎብኙ፡ **https://www.waproviderone.org/client**
- ከክፍያ ነፃ መስመር ላይ ይደውሉ፡1-800-562-3022
- በመስመር ለቅያር ይጠይቁ፡ **https://fortress.wa.gov/hca/p1contactus/home/client**
    - o "Services Card” የሚለውን ርዕስ ይምረጡ።

**ይህ የ ProviderOne አገልግሎቶች ካርድዎ ነው።**



### በጤና እቅድዎ ሰጪ ተቋም ዘንድ መመዝገብ

በ **wahealthplanfinder.org** በኩል ለApple Health ካመለከቱ፤ ምናልባትም በአቅራቢያዎ በሚገኝ በአንዱ የጤና እቅዶች ተመድበዋል። እርስዎ በወቅቱ በጤና እቅድ ካልተመዘገቡ እኛ አንዱን እንመርጥልዎታለን።

### የጤና እቅዴን መለወጥ እችላለሁ?

በየትኛውም ጊዜ የጤና እቅድዎን መቀየር ይችላሉ። ለውጥ ሲደረግ፣ ለውጡ የተደረገበት ጊዜ ላይ ተመስርቶ፣ ብዙ ጊዜ በቀጣዩ ወር የመጀመሪያ ቀን ላይ ይጀምራል። የእቅድ ሰጪዎትን ለመቀየር ብዙ አማራጮች ይኖሮታል፡

- ኦንላይን፡- **wahealthplanfinder.org**
- ProviderOne ደንበኛ ፖርታል: **https://www.waproviderone.org/client**
- በመስመር ለመቀየር ይጠይቁ፡ **https://fortress.wa.gov/hca/p1contactus/** ። “Client” (ደንበኛ) የሚለውን በመምረጥ “Enroll/Change Health Plans” (“ምዝገባ/የጤና እቅዶች ለውጥ”) የሚለውን ርዕስ ይምረጡ።
- ለኛ የደንበኛ አገልግሎት ማዕከል ይደውሉ በ1-800-562-3022 ላይ።




Washington State Health Care Authority
የጤና ክብካቤ ባለሥልጣን Washington Apple Health (Medicaid)ያስተዳድራል።


| የሚተዳደር የእንክብካቤ ጤና* | ስልክ | የነርስ የእርዳታ መስመር* |
|---|---|---|
| Community Health Plan Of Washington (CHPW)<br>**chpw.org** | 1-800-440-1561 | 1-866-418-2920 |
| Coordinated Care of Washington, Inc (CC)<br>**coordinatedcarehealth.com** | 1-877-644-4613 | 1-877-644-4613 |
| Molina Healthcare of Washington (MHW)<br>**molinahealthcare.com/members/wa** | 1-800-869-7165 | 1-888-275-8750 |
| UnitedHealthcare Community Plan (UHC)<br>**uhccommunityplan.com/wa/medicaid/imc** | 1-877-542-8997 | 1-877-543-3409 |
| Wellpoint Washington (WLP)<br>**wellpoint.com/wa/medicaid** | 1-833-731-2167 | 1-866-864-2544 |


* ሁሉም እቅዶች በግዛቱ ሁሉም ቦታዎች አይገኙም።


** ነርስን ለማነጋገር ከፈለጉ፣ በቀን ለ24 ሰዓት፣ በሳምንት ለሰባት፣ የጤና እቅድዎ የነፃ መስመር ላይ ይደውሉ።




## የጤና እቅድዎ ካርድ

የጤና እቅድዎ በዚህ ገፅ ላይ ከታዩት አንዱን የሚመስል የመለያ ካርድ ይልልዎታል። ይህንን ካርድ ይያዙ። ሀኪም ለማየት፣ ፋርማሲ፣ ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋ በሚሄዱባት ወቅት ሁለቱንም የProviderOne አገልግሎቶች እና የጤና እቅድዎን ካርዶች ይያዙ። ፎቶ ያለበት መታወቂያም ሊያስፈልግዎ ይችላል።

## በWashington Apple Healthና Medicaid መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

Washington Apple Health በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ የMedicaid ስም ነው። የእርስዎ የጤና እርዳታ ሰጪ ወይም እግዳ ተቀባዩ Medicaid ብለው ሊጠሩት ይችላሉ።

## ቁጥጥር የሚደረግበት ሕክምና ምንድነው?

አብዛኛዎች የApple Health ደንበኞች "የሚተዳደር እንክብካቤ" ("managed care" ) አላቸው፣ ማለትም ወራዊ ለጤና እቅድዎን ክፊያ ሽፋን የApple Health ይከፍልል።

## የሚተዳደር የእንክብካቤ እቅድ ውጭ የሆነ የApple Health ምንድነው?

የሚተዳደር የእንክብካቤ እቅድ ውጭ የሆነ የApple Health ሽፋን (የአገልግሎት-ክፊያ በመባል የሚታወቅ) ማለት የApple Health በቀጥታ ለአቅራቢዎ ሲከፍል ማለት ነው። አብዛኞች የApple Health ደንበኞች በሚተዳደር እንክብካቤ ነው የሚሳተፉት።

በሚተዳደር እንክብካቤ የሚሳተፉ ቢሆኑም፣ የApple Health አቅራቢዎን ለተወሰኑ ጥቅማጥቅሞች በቀጥታ ከፍላል። ይህም የአገልግት- ክፊያይባላል።

ከሚተዳደር የእንክብካቤ እቅድ ውጭ በApple Health የሚሳተፉ ደንበኞች አቅራቢን በመስመር በዚህ ማግኘት ችላሉ: **https://fortress.wa.gov/hca/p1findaprovider** ወይም ይደውሉ 1-800-562-3022።

## የProviderOne አግልግሎቶች ካርዴን ከማግኘቴ በፊት አገልግሎቶችን ለማግኘት እችላለሁ?

ካርድዎ ከመድረሳቸው በፊት በዚህ ዶክተሮችን ለማየት ወይም የመድሃኒት ማዘዣቆችን ለመሙላይ ይችላሉ:

- የProviderOne የመለያ ቁጥርዎን ለማግኘት፣ የProviderOne የደንበኛ ድረ-ገፅን ይመልከቱ እዚህ **https://www.waproviderone.org/client**። ያንን ቁጥር ለጤና እርዳታ ሰጪ ወይም ፋርማሲስት ይስጡ።
- ለአቅራቢው ወይም ለፋርማሲሰቱ ስምዎን፣ የትውልድ ቀን እና የማህበራዊ ደህንነት ቁጥርዎን ይንገሩ። እነሱም በሲሰተሞቹ ውስጥ እርስዎን ለማየት ይችላሉ።

## እኔ የጤና እቅድ ካርዴን ከጣልኩ ምን ይፈጠራል?

- ለጤና እቅድዎ በመደወል አዲስ ካርድ እንዲሰጥዎት ይደውሉ።

## የApple Health ተሳትፎዬን እንዴት ማየት እችላለሁ?

የApple Health ተሳትፎዎን ይመልከቱ:

- መስመር ላይ (ኦንላይን):- **https://www.waproviderone.org/client**
- ስልክ:- 1-800-562-3022

## እኔ በጤና እቅድ መመዝገብ አለብኝ?

አዎ፣ ከጥቂት ማግለያዎች ጋር በጨማሪ ዝርዝር ለማየት በመስመር ላይ የእንኳን በደህና መጣችሁ ቡክሌትን ይመልከቱ: **hca.wa.gov/ah-client-booklets**። የትኛውን ቡክሌት ማንበብ እንዳለቦት እርግጠኛ ካልሆኑ በ1-800-562-3022 ለ Apple Health የደንበኞች አገልግሎት ማእከል ይደውሉ።

## የትኛውንም አቅራቢ ለማየት እችላለሁ?

አይ፣ እቅድዎ እስፔሻልስትእንዲያገኙ የፅሁፍ ፈቃድ ካልሰጠዎት በስተቀር፣ በጤናዎ እቅድ አውታረ መረብ (ኔትዎርክ)ውስጥ ያሉትን አቅራቢ ማየት አለብዎት። የተለየ አቅራቢን መጠቀም ከፈለጉ፣ የትኛው የጤና እቅዶች አውታረ መረብ ውስጥ እንደሆኑ ይጠይቁ።

## በቤተሰቤ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ግለሰብ ተመሳሳይ የጤና እቅድ አለው?

አዎን፣ ሂንዲያን ወይም የአላስካ ተወላጅ ካልሆኑ በስተቀር፣ አሜሪካዊ በቤተሰብዎ ሁሉም ሰው ተመሳሳይ የጤና እቅድ ነው ያለው።

## በእቅዶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

ሁሉም እቅዶች ተመሳሳይ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ይሸፍናሉ፣ ነገር ግን አገልግሎቶችን የሚያቀርቡበት መንገድ እና የአቅራቢያቸው አውታረ መረብ ይለያያል።

- ስለ መሰረታዊ የተሸፈኑ አገልግሎቶች የበለጠ ይወቁ: **hca.wa.gov/apple-health-services**።

## ሽፋኔን እንዴት ነው የማድሰው?

በአብዛኛው ጊዜ የእርስዎ የApple Health ሽፋን ለአንድ ዓመት ይቆያል። ሽፋንዎን እንዲያድሱ ለማስታወስ ደብዳቤ እንልክልዎታለን፣ ስለዚህም የፖስታ አድራሻዎን ማዘመን አስፈላጊ ነው። እንዴት ሽፋንዎን ኦንላይን ላይ እንዲሚያድሱ የበለጠ ይማሩ በዚህ **hca.wa.gov/apply-or-renew-coverage**።

## እኔ የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን ካለኝ ምን ላድርግ?

በቀጣሪዎ፣ በባለቤትዎ/በጓበኛዎ፣ ወይም በቤተሰብ በኩል ሌላ የህክምና ወይም የጥርስ ሽፋን የሚያገኙ ከሆነ፣ የApple Health ተገቢው የሽፋን አገልግሎቶች፣ የተቀናሽ፣ የጋራ-ክፊያ እና ከክስ ለተከፈለ ክፊያ ይከፍላል።
ከሚከተሉት በአንዱ ሌላውን የጤና እንክብካቤ ሽፋንዎን ሪፖርት ያድረጉ:

- መድህነ ወይም በመስመር ለውጥን በዚህ ሪፖርት ያድርጉ **https://fortress.wa.gov/hca/p1contactus/**.።
- Apple Health Customer Service በማለት ወደ 1-800-562-3022 ይደውሉ።

በሚተዳደር የእንክብካቤ እቅድ ከተሳተፉ፣ እንዲሁ ለእቅደዎ ሌላኛውን መድህንዎን ሪፖርት ያድርጉ።

## የትኛውን ፋርማሲ ወይም የመድሃኒት መደብር እጠቀማለሁ?

በጤና እቅድዎ አውታረ መረብ ውስጥ ያሉ ፋርማሲዎችን ወይም የመድሃኒት መደብሮችን ይጠቀሙ።

## እኔ ድንገተኛ የጤና ችግር ካለብኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

ድንገተኛ ወይም ድንገተኛ ነው ብለው የሚያስቡት ከባድ የጤና ችግሮች ሲያጋጥምዎ፣ ለ911 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደ ሚገኝ የድንገተኛ ክፍል ይሂዱ። ድንገተኛ እንዲጋጠመዎ እና እንክብካቤውን ከየት እንዳገኙ በተቻለ መጠን በፍጥነት ለጤና እቅድዎ ይደውሉ።

እርስዎ አስቸኳይ ህክምና ከፈለጉ ነገር ግን ለህይወትዎ የማሰጋ ከሆነ ለመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪዎ፣ ለጤና እቅድዎ ወይም የ24 ሠዓት የነርስ እርዳታ መስመር ይደውሉ፡ ስልክ ቁጥሮች ለማግኘት ገጽ 2 ይመልከቱ።

## እኔ የጤና እርዳታ ሰጪ ጋር ሄዶ ለመታከም ወይም የመድሃኒት ማዘዣዎች ለመሙላት መክፈል አለብኝ?

አይ፣ ለተሸፈነ አገልግሎት መክፈል አይጠበቅብዎም። እርስዎ ክፍያ የሚከፍሉት፡

- እንደ ኪሮፕራክትክ እንክብካቤ ወይም የቁንጅና ቀዶ ህክምና ያሉ ሽፋን የሌላቸው ወይም በህክምና አስፋላጊ አገልግሎትን ነው ያገኙት።
- ለአቅራቢዎ የጤና ሽፋን መረጃን አልሰጡም።
- ድንገተኛ ካልሆነ ወይም በጤና እቅድዎ በቅድሚያ ሳይፈቀድ፣ በጤና እቅድዎ አውታረ መረብ ውስጥ ከሌለ አገልግሎት አቅራቢ እንክብካቤን አግኝተዋል።
- ከእስፔሻሊስት እንክብካቤ ለማግኘት የጤና እቅድ ህግጋቶችን አልተከተሉም።

በአገልግሎት ክፍያ ዜዴ የሚሰራ አገልግሎት ሰጪ ለማፈላለግ ProviderOne Find a Provider search tool **https://fortress.wa.gov/hca/p1findaprovider**ይመልከቱ።

በApple Health በቀጥታ ለሚከፍሉ ዝርዝር ጥቅማ ጥቅሞች፣ በኦላይን በሚገኘው ወደ የዋሽንግተን የApple Health እንኳን በደህና መጣችሁ ቡክሌት ላይ፣ ይመልከቱ እዚህ፡ **hca.wa.gov/ah-client-booklets**።

## የጥርስ ህክምና እንዴት አገኛለሁ?

የጥርስ እንክብካቤን የApple Health ከተቀበለው አቅራቢያ ያገኛሉ። ለየአገልግሎት-ክፍያ አቅራቢን ለማግኘት የአቅራቢ መፈለጊያ መሳሪያን ይጠቀሙ። የጥርስ አገልግሎቶችን በሚያገኙበት ወቅት የProviderOne አገልግሎቶችን ካርድ ይጠቀሙ።

የጥርስ ህክምና አቅራቢን ለመፈለግ፡

- DentistLink (ዴንትስሊንክ)
    - ኦንላይን: **DentistLink.org**
    - 1-844-888-5465 ላይ ይደውሉ
- የአቅራቢ መፈለጊያ መሳሪያ ፈልጉ፡
    - ኦንላይን: **https://fortress.wa.gov/hca/p1findaprovider**

በApple Health የተሸፈኑ የጥርስ ህክምና አገልግሎቶችን አጠቃላ እይታ ይመልከቱ በዚህ **hca.wa.gov/dental-services**።

## የአይን ምርመራን እና መነፀርን እንዴት አገኛለሁ?

ነፀብራቅ እና የእይታ መስኮችን ጨምሮ፣ ተስማሚ አገልግሎቶች እና የአይን ምርመራዎች፣ ለህጻናት እና ለአዋቂዎች በጤና እቅድዎ በኩል ሊሰጡ ይችላሉ።

- እድሜያቸው 20 አመት እና ከዚያ በታች ለሆኑ ልጆች- የአይን መነፅር ክፈፎች፣ ሌንሶች እና የመገናኛ ሌንሶች በApple Health ክፊያ - ለአገልግሎቶተች ይሸፈናሉ፡ ፡ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ አቅራቢዎ እነዚህን ጥቅማ ጥቅሞች ለመፈለግ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንክብካቤዎን በማቀናጀት ይረደዎታል።
- ለአዋቂዎች- የመነፅር ክፈፍ፣ ሌንሶች እና የመናኛ ሌንሶች በApple Health አይሸፈኑም። የአይን መነፅር ፍሬሞችን እና ሌንሶችን ተሳታፊ አቅራቢን በሚከተለው በማግኘት በቅናሽ ዋጋ መግዛት ይችላሉ **hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/optical_providers_adult_medicaid.pdf**።

## ሌላ ምን ማወቅ ያስፈልገኛል?

ወደ ዋሽንግተን Apple Health እንኳ በደህና መጡ ቡክሌት ውስጥ የተካተቱ ተጨማሪ መረጃ በመስመር ላይ በ**hca.wa.gov/ah-client-booklets** እና ከጤና እቅድዎ ከተቀበሉት ቁሳቁሶች ውስጥ ይገኛል።

| አስፈላጊ ድረ-ገፆች | |
|---|---|
| **ድህረ-ገጽ** | **URL** |
| Apple Health | **hca.wa.gov/apple-health** |
| ProviderOne የደንበኛ ፖርታል | **https://www.waproviderone.org/client** |
| Washington Healthplanfinder | **wahealthplanfinder.org** |
| Washington Connection | **washingtonconnection.org** |
| እንኳን ወደ Washington Apple Health ቡክሌትበደህና መጡ | **hca.wa.gov/ah-client-booklets** |